# ጥናት አንድ ራዕ 2፡1-7 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ ይህንን ሲል አብያተ ክርስትያናቱ በሙሉ በእርሱ እጅ ውስጥ እንዳሉና እርሱ ሙሉ በሙሉ እንደሚቆጣጠራቸው ሲያሳይ፤ የኤፌሶን ቤተ ክርስትያን እየለፋችና እየሰራች ያለችው ነገር ሁሉ ከእርሱ የተሰወረ እንዳልሆነና ሁሉንም እንደሚያይ ሲገልጽ ነው።
2. ኢየሱስ የዚህችን ቤተ ክርስትያን ሥራዋን ያውቃል፣ ድካምዋን ያውቃል፣ ክፉዎችን ልትታገስ እንደማትችል፣ ሐዋርያት ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን የሚሉትን መርምራ ታውቃለች፣ ትዕግሥት እንዳላትና ስለስሙም ጸንታ እንደቆመች ሁሉ ያውቃል።
3. ይህች ቤተ ክርስትያን ያለችበትን ሁኔታና ኢየሱስ የዘረዘራቸውን ነገሮች ሁሉ ስንመለከት፤ ቤተ ክርስትያኒቱ ምንም ተጨማሪ ነገር እንደሚያስፈልጋት አድርጎ ለማየት ያስቸግራል፤ ስለዚህም ጉድለት ያለባት ቤተ ክርስትያን አድርጎ ሰው የሚያያት አይመስለኝም፤ ለኢየሱስ ግን በልብ የሚቀጣጠል ፍቅርን ካላየ ሌላው ነገር ብቻ አይበቃውም።
4. ‹‹የምነቅፍብህ ነገር›› በማለት በቁ4 ላይ የሚናገረው ነገር ቀድሞ የነበራትና አሁን የጣለችው ነገር እንዳለ፤ ይህም ደግሞ የቀድሞ ፍቅር በማለት ይናገራል። ኤፌሶን ቤ/ክ ብዙ መልካም ነገሮች እያላት ኢየሱስ አንዱን ጉድለት ያጎላበት ምክንያት፤ ፍቅር ከሌለኝ እንደሚንሸዋሸው ጸናጽል ነኝ እያለ በ1ኛ ቆሮ 13 ላይ ሐዋርያው እንደሚናገር ያለፍቅር ነገር ሁሉ ከንቱ ስለሆነ ነው።
5. ቤተ ክርስትያኒቱ እንድትወስድ የተነገራት እርምጃዎች፤ ከወዴት እንደወደቀች እንድታስብ፣ ንስሃ እንድትገባና ተመልሳም የቀደመውን ሥራዋን እንድታደርግ ነው። እነዚህ ይህች ቤተ ክርስትያን እንድትወስድ የተነገሩት እርምጃዎች ማናቸውም ሰው ከመስመር ሲወጣና ሲስት ተመልሶ በነበረበት ሥፍራ መገኘት ከፈለገ ማድረግ የሚገባው ነገሮች ናቸው።
6. የኤፌሶን ቤተ ክርስትያን ምክሩን ለመመለስ እንቢ ብትል ኢየሱስ መጥቶ መቅረዙን ከሥፍራው እንደሚወስድ ነው የሚያስጠነቅቃት። ምንም እንኳን ለዚህች ቤተ ክርስትያን ጎደለ የተባለው ነገር አንድ ብቻ ቢሆንም፤ ይህ የጎደለው ነገር በተለይም በእግዚአብሄር ዓይን ዋነኛ አድርጎ ከሚያያቸው ነገሮች አንደኛና ዋነኛው ነው።
7. ኢየሱስ ለአብያተ ክርስትያናቱ የሚናገረውን ነገር ጆሮ ያላቸው ሁሉ እንዲሰሙት ነው። ይህንን አነጋገሩን ስንመለከት እኛም የምንጠቃለልበት ምክንያት እኛም የሚታየው የሥጋ ጆሮ ብቻ ሳይሆን የልብ ጆሮዎቻችንን እግዚአብሄር ስለከፈተልን ለመስማትና ከትምህርቱ ልናተርፍበት እንችላለን።
8. በዚህ ዓውደ ጥናት መሰረት ድል መንሳት የሚለው ሃሳብ የወደቁበትን አውቆ፣ ንስሃ በመግባት የቀደመውን ሥራ ለማድረግ መጀመርን ነው።
9. እያንዳንዱ በልቡ የተሰማውን እንዲናገር ጊዜ ይሰጠው።

# ጥናት ሁለት ራዕ 2፡8-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጌታ በዚህ ክፍል ውስጥ ራሱን የሚያስተዋውቀው ‹‹ሞቶ የነበረው ህያውም የሆነው፤ ፊተኛውና መጨረሻው›› በማለት ነው፡፡
2. ኢየሱስ ሞቶ እንደነበረና ነገር ግን አሁን ህያው እንደሆነ መናገሩ እርሱ በስንት ጣር፣ ጭንቅና መከራ በመስቀል ሞት ሁሉ አልፎ ለዚህ የዘላለም ክብር እንደበቃ ሁሉ፤ ይህች የሰምርኔስ ቤተ ክርስትያንም በእርሱ ምክንያት በምታልፍበት ታላቅ መከራ አልፋ ለክብር ሊያበቃት እንደሚችል ሲያሳስባት ነው እላለሁ፡፡
3. ስለቤተ ክርስትያኒቱ ጌታ አውቃለሁ የሚላቸው ሁለት ነገሮች፤ አንደኛው መከራዋ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ድህነት ናቸው፡፡ ድሃ የሚለው ሃሳብ ምናልባትም በሥጋ የሚገኙበትን ሁኔታ ሲሆን፤ ባለጠግነቱ ግን ከመንፈሳዊ ህይወት ጋራ የተገናኘ በክርስቶስ ያገኙት በረከትና ባለጠግነት ስለሆነ ሁለቱ የሚቃረኑ ሃሳቦች አይደሉም፡፡
4. በእኛ ዘመን ምናልባትም አማኞች ሳይሆኑ አማኞች ነን በማለት ራሳቸውንና ሰዎችንም ለማታለል የሚሞክሩትን ሊሆን ይችላል ብዬ አምናለሁ፡፡ በቤተ ክርስትያን መሃል ሁሉም ስንዴ እንደሆነ ከማሰብ ይልቅ ጌታ እንዳለ ገለባም እንደሚኖር ማወቁ ለመጠንቀቅም ሆነ ያልሆኑ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ሰዎች እንዳይበረግጉና እንዳይደናገጡ ይጠቅማል፡፡
5. ለቤተ ክርስትያኒቱ የሚሰጣት ማስጠንቀቂያ መከራ የምትቀበልበት ጊዜ እንደደረሰና ዲያቢሎስ ለአስር ቀናት ወህኒ ሊያስገባቸው እንደሆነ ነው፡፡ ጌታ ልጆቹን ከመከራ የሚከልልባቸው ጊዜያት እንዳሉ ቢታወቅም ነገር ግን ሁልጊዜ ሥራው ከመከራ መከለል ሳይሆን በመከራም ውስጥ እንዲያድጉና እርሱን ለመምሰል የሚበቁበትን ሁኔታ ማመቻቸት ስለሆነ ነው፡፡
6. ይህ በዚህች ቤተ ክርስትያን ላይ እንደሚደርስ የተነገረው መከራ፤ ዲያቢሎስ ቅዱሳንን ለመፈተን የሚያመጣውና ወደ እስር ቤት የሚጥልበት ሁኔታ ነው፡፡ ኢየሱስ ይህ ሁሉ ገና ሳይፈጸም አስቀድሞ መናገር መቻሉ የሚያሳየን አምላክ እንደሆነና ሰው ሊያውቀው የሚችለውን ሁሉ እንደሚያውቅ ነው፡፡
7. በመከራው ስስጥ ከምታልፈው ቤተ ክርስትያን የሚጠበቀው ነገር በቁ10 ላይ እንደምናየው እስከሞት ድረስ ታማኝ ሆኖ መገኘት ሲሆን፤ ከኢየሱስ ክርስቶሰ የሚጠበቀው ደግሞ ታምኝነታቸውን አክብሮ የህይወት አክሊልን እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቷል፡፡
8. ይህችን ቤተ ክርስትያን አስመልክቶ ደግሞ ድል መንሳት የሚለው ሃሳብ የሚጠቁመን፤ ምንም እንኳን የተሸነፈች የምትመስል ቤተ ክርስትያን ብትሆንና በእስር ቤትም ውስጥ የሞት እጣ ቢገጥማቸው፤ እንደነዚህ ያሉት ሰዎች ድል አድራጊዎች ስለሆኑ በሁለተኛውና በአስፈሪው ሞት አይጎዱም ወይም የእነርሱ የእጣ ክፍል አይሆንም ማለት ነው፡፡
9. በየግል የሚመለስ ጥያቄ ነው፡፡

# ጥናት ሶስት ራዕ 2፡12-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ ለጴርጋሞን ቤተ ክርስትያን ራሱን ያስተዋወቀው በሁለት በኩል የተሳለ ስለታም ሰይፍ እንዳለው ነው። ኢየሱስ በሁለት በኩል የተሳለ ስለታም ሰይፍ እንደያዘ ለዚህች ቤተ ክርስትያን ማስተዋወቁ አደገኛ በሆነ ሰይጣን ራሱ ዙፋኑን በዘረጋበት መሃል እንደሚገኝ ስለሚናገር፤ ኢየሱስ ተዋጊና ባለሰይፍ ሆኖ ራሱን ማሳየቱ ለማበረታታት ትልቅ ቦታ አለው ብዬ አምናለሁ።
2. ይህች ቤተ ክርስትያን ያለችበት ሁኔታ ከጌታ የተሰወረ እንዳልሆነ ማሰገንዘቡና ያለችበትን ሁኔታ ማወቁ፤ ያለ እርሱ እውቀት በማትታይበት ቦታ ይዞ ጠላት የሚደቁሳት ሳይሆን እግዚአብሄር የሚቆጣጠረው፣ በእርሱ ተጣርቶ ያለፈ ነገር መሆኑን ማወቅ መጽናናት ይሆናል። እኛም ብንሆን የምናልፍባቸው ሁኔታዎች ከጌታ የተሰወሩ እንዳልሆኑ ልንረዳ ያስፈልገናል።
3. የጌታ ልጆች በማናቸውም አይነት ከባድና አደገኛ በሆነው የጠላት ሰፈር እንኳን በእርሱ ብርታት ሊኖሩ ይችላሉ። ከዚህ ክፍል እንደምናየውም የሚኖሩበት ሁኔታና ሥፍራው መክበዱንም እንኳን ቢያውቅም፤ ከዚያ የተነሳ የመንፈሳዊ ህይወት ጥራቱ ዝቅተኛ እንዲሆን ብሎ የሰጣቸው ነገር አንመለከትም፤ ማለትም ህይወታችን በየትኛውም ሥፍራ ብንሆን የቅድስናን የጽድቅ ህይወት ሊሆን ይገባል።
4. ጌታ የሱስ የሚነቅፍባቸው ሁለት ነገሮች፤ አንደኛው ባላቅን ያስተማረውን የበለዓምን ትምህርት የሚከተሉ ሰዎች በመሃሉ ዝም ብሎ ማኖሩ፣ ሁለተኛው ደግሞ የኒቆላውያንን ትምህርት የሚከተሉም ሰዎች በመሃላቸው ዝም ተብለው ይገኛሉ የሚሉት ናቸው።
5. የበለዓም ትምህርት በመባል በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው ነገር፤ በዘኍ 31፡15-16 ላይ እንደምናነበው እርግማን ሊያገኘው ያልቻለውን የእግዚአብሄር ህዝብ በራሱ ምኞትና እንቢተኛነት ሽንፈት ውስጥ እንዲወድቅ ለማድረግ ምን ማድረግ እንደሚችል ለባላቅ የሰጠውን ምክር ነው።
6. በጴርጋሞን ቤተ ክርስትያን ውስጥ የማያቸው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እምነታቸውን ጠብቀው የሚኖሩ፣ የበለዓምን ትምህርት ወይም የሐጥያት ኑሮን ለማስተናድ ወደኋላ የማይሉና፣ የኒቆላውያንን ትምህርት የሚከተሉ፤ ማለትም ሶስት ዓይነት ሰዎችን አያለሁ።
7. ቤተ ክርስትያኒቱ በቁ16 ላይ እንድታደርግ ስትጠየቅ የምናየው ንስሐ እንድትገባ ነው። ይህንን ማስጠንቀቂያ ተቀብላ በንስሃ መመለስ እንቢ ብትል ግን የሚያገኛት ነገር በአፉ ስለታም ሰይፍ መወጋት እንደሆነ እናነባለን።
8. እያንዳንዱ በግሉ የሚሰማውን ይናገር።

# ጥናት አራት ራዕ 2፡18-29 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በትያጥሮን ስለምትገኘው ቤተ ክርስትያን ጌታ የሚያውቃቸው ነገሮች፤ ሥራዋን ያውቃል፣ ፍቅሯን ያውቃል፣ እምነቷን ያውቃል፣ አገልግሎቷንና ትዕግሥቷን ሁሉ የሚያውቅ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ከመጀመሪያው ሥራዋ ይልቅ የአሁኑ እንደሚበልጥም ያውቃል፡፡
2. የዚህች ቤተ ክርስትያን ዋነኛ ድክመት ሆኖ የተነገረው ነገር ነብይ ነኝ ባይዋን ኤልዛቤል ችላ ብላ መተዋ ነው፡፡ ኤልዛቤል የጌታ አገልጋዮች እንዲሴስኑ የምታደርግና ለጣዖት የተሰዋውን እንዲበሉ የምታስተምር ነች፡፡
3. ኢየሱስ በዚህች ኤልዛቤል በተባለችው ሴት ላይ የወሰደው እርምጃ ንስሃ እንድትገባ እድል መስጠት ሲሆን፤ እርሷ ግን በዚህ እድል ስላልተጠቀመችበት በመከራ አልጋ ላይ እንደሚጥላት፣ ከእርሷ ጋራ የሚያመነዝሩትም ካልተመለሱ ብርቱ ሥቃይ እንደሚያመጣባቸው፣ ልጆችዋንም ደግሞ በሞት ይቀጣቸዋል፡፡ ለዚህች ሴት እንኳን የንስሃ እድል መስጠቱ የጌታን ቸርነትና በጎነት ያስተምረናል፡፡
4. በዚህች ቤተ ክርስትያን ውስጥ ኤልዛቤልን አስመልክቶ ትምህርቷን ሆነ ብለው የሚከተሉና አኗኗራቸውን ያረከሱ ሰዎች ሲኖሩ፤ ሌሎቹ ደግሞ ትምህርቷንም ሆነ አኗኗሯን ሳይከተሉ በቅድስና የሚኖሩ እንዳሉ ቁ24 ላይ እናነባለን፡፡
5. በቁ23 ላይ የኤልዛቤል ልጆች አድርጎ የሚናገራቸው ትምህርቷንና ሥራዋን ተከትለው የሚኖሩትን ሰዎች ነው፡፡ በኤልዛቤል መንገድ የሚሄዱትን በመግደል ጌታ ለቅዱሳን ማስተማር የሚፈልገው ነገር፤ ሃጥያት ለጊዜው ቅጣት የሌለው ነገር ሆኖ ቢቆይም እንኳን ጽዋው ሲሞላ የሃጥያት ደመወዙ ሞት እንደሆነ ሊያስረግጥላቸው ነው፡፡
6. ከዚህ አነጋገሩ ስለ ጌታ ባህርይ መማር የምንችለው አንድ እውነት የክርስትና ህይወታችንን በበጫና ከብዶብን እንድንኖር የሚፈልግ እንዳልሆነ የሚያሳየን ሲሆን፤ ሰዎች ግን ብዙ ጊዜ ክርስትና የሚያስጨንቅና ጫና የበዛበት ህይወት እንደሆነ ነው ሲናገሩ የሚሰማው፡፡
7. ‹‹ነብይ ነኝ የምትለዋን ሴት…›› ከሚለው አነገገር መማር የምንችለው፤ ሰዎች ራሳቸውን ነብይ ብለው ከመጥራት የሚከለክላቸው ነገር እንደሌለና ይህ ማለት ግን እግዚአብሄር የተቀበላቸው እውነተኛ ነብያት ናቸው ማለት ላይሆን እንደሚችል እንረዳለን፡፡
8. ይህች ቤተ ክርስትያን ፍቅርን ይዛ የዶክትሪን ጥራት የጎደላት እንደሆነ ስናይ፤ የኤፌሶን ቤተ ክርስትያን ደግሞ በተቃራኒው የተጣራ ዶክትሪን ይዛ ነገር ግን የፍቅር ጉድለት የሚታይባት ቤተ ክርስትያን እንደሆነች እንመለከታለን፡፡
9. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይናገር፡፡

# ጥናት አምስት ራዕ 3፡1-6 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በሰዎች አይን ስትታይ የሰርዴስ ቤተ ክርስትያን ህይወት ያላትና ጎላ ብላ የምትታይ ስትሆን፣ በጌታ ዓይን ስትታይ ግን ምውትና ህይወት የሌለባት እንደሆነች ይነግረናል። እንደዚህ ሰፊ የሆነ ልዩነት የምናይበት ምክንያት፣ ሰው የውጭውን ስለሚያይና ሰውንም ማታለል ቀላል ስለሆነ ሲሆን፣ ጌታ ግን የውስጥን ስለሚያይ የተሰወረው ሁሉ በርሱ ፊት የተገለጠ ስለሆነ ነው።
2. ‹‹ሞተሃል›› የሚለው አነጋገር እኛ ሞት ብለን በምንረዳው የሥጋ ሞት ሳይሆን ልክ ኤፌ 2 ላይ የምናየው ሞት ስለሆነ፣ መንፈሳዊ እንቅልፍ ማለትም ድካምንና በህይወት መዛልን የሚያሳይ አነጋገር ነው።
3. በቁ2 ላይ ነቅቶ እንዲያደርግ የተነገረው ነገር ሊሞት የተቃረበውን ነገር እንዲያጸና፣ የተቀበለውን፣ የሰማውን እንዲያስታውስ ስለዚህም ይህንን የተነገረውን ነገር በመታዘዝ ንስሃ እንዲገባ ነው የተነገረው። በህይወታችን ሊሞቱ የደረሱት ነገሮች ላይ ህይወት ለመዝራት የሚያስፈልገን ነገር መንቃትና ንስሃ መግባት ነው።
4. የሰው ሁሉ ሥራ የሚመዘነው በእግዚአብሄር ሚዛን ላይ እንደሆነ ነው በዚህ ክፍል ኢየሱስ የሚነግረን፣ ስለዚህም ሰውን ደስ የሚያሰኘውንና በሰዎች አይን ተቀባይነት ያለውን ለማድረግ ከመሞከር ይልቅ በእግዚአብሄር ሚዛን ተመዝኖ የሚያልፍ ነገር ላይ ልናተኩር ይገባናል።
5. የምንሰማውንና የተቀበልነውን የእግዚአብሄር ቃል በእውቀት ደረጃ ብቻ ይዘነው በአእምሮአችን የምናቆየው ነገር ብቻ ሳይሆን የምንታዘዘውና የምንኖርበት፣ ለንስሃም የሚያበቃን እውነት ሊሆን ይገባል።
6. የሰርዴስ ቤተ ክርስትያን የተሰጣትን ማስጠንቀቂያ ባትቀበልና ችላ ብትል፣ ኢየሱስ በምን ሰዓት እንደሚመጣ በማታውቅበት ሁኔታ እንደ ሌባ እንደሚመጣባት እናነባለን።
7. በዚህች ቤተ ክርስትያን ያሉትን ለሁለት የከፈለው፣ አንደኛዎቹ በስማቸው ወይም በሰው ፊት ህያዋን ሆነው የሚታዩ ነገር ግን ሙታን የሆኑና፣ ሌሎቹ ደግሞ ልብሳቸውን ያላሳደፉ ጥቂት ሰዎች በማለት ይከፍላቸዋል። ከዚህ የምንማረው የጌታን እውነት መያዝ እንጂ በቁጥር ማነስ ለጊዜው ተሸናፊነት ቢመስልም በቁጥር መብዛት ግን ሁልጊዜ የትክክለኛነት ምልክት እንዳልሆነ ልናውቅ ይገባናል።
8. አማኝ ድል ነሳ ማለት በዚህ ዓውደ ምንባብ መሰረት፣ ጌታ የነገረውን የእርማት ቃል በመስማትና በመታዘዝ ከሞተው መንፈሳዊ ህይወት በመንቃት ንሰሃ ገብቶ ወደሚፈለግበት ቦታ መመለስን ነው የሚያመለክተው።
9. እያንዳንዱ ሰው የራሱን መልስ ይስጥ።

# ጥናት ስድስት ራዕ 3:7-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ ለዚህች ቤተ ክርስትያን ራሱን የሚያስተዋውቅባቸው ሶስት ነገሮች፤ ቅዱስና እውነተኛ የሆነው፣ የዳዊትን መክፈቻ በእጁ የያዘውና፣ እርሱ የከፈተውን ማንም ሊዘጋው አይችልም፣ እርሱ የዘጋውንም ማንም ሊከፍት አይችልም በሚል ነው የሚያስተዋውቀው።
2. ስለፊላደልፊያ ቤተ ክርስትያን ኢየሱስ አውቃለሁ የሚላቸው ነገሮች፤ ሥራህን አውቃለሁ፣ ሃይልህ ትንሽ እንደሆነ አውቃለሁ ነው የሚላት።
3. ይህች ቤተ ክርስትያን በኢየሱስ በራሱ የተከፈተ በፊቱ እንዳደረገለት በቁ8 ላይ ሲነግር እናነባለን፤ ስለዚህም ይህች ቤተ ክርስትያን ይህንን የኢየሱሰ ስጦታ የሆነውን የተከፈተ በር ሰይጣንም ሆነ ማንኛውም ሃይል ሊዘጋባት እንደማይችል ማረጋገጫ ነው የሚሰጣት።
4. ሃይላችን ትንሽ እንደሆነና ማድረግ የምንችለው ነገር ውስን እንደሆነ ጌታችን ማወቁ ለእያንዳንዳችን ትልቅ መጽናናት ነው፤ ይህንን ስለሚያውቅ ከእርሱ ማለቂያ ከሌለው በታላቅ ሃይሉ የሚያስፈልገንን ሁሉ መሙላት ስለሚችል መልካም ዜና ነው። ቃሉን ለመጠበቅ ማንም ቢሆን በራሱ ሃይል ስለማይችል የእርሱ ሃይልና ብቃት የግድ ለደካሞቹ ለእኛ አስፈላጊነቱን እያንዳንዳችን ልንቀበል ይገባናል።
5. አንደኛው ማንም ሊዘጋው የማይችለው የተከፈተ በር ሰጥቷታል፣ ሁለተኛው ደግሞ አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን በማለት የሚዋሹትን ከእግሯሥር እንዲመጡ እርሱ እንደወዳትም እንዲያውቁ አድርጓል፣ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ በምድር ላይ የሚኖሩትን ሊፈትናቸው በዓለም ሁሉ ከሚመጣው ፈተና መጠበቅ ናቸው።
6. ኢየሱስ በቁ11 ላይ የፊላደልፊያን ቤተ ክርስትያን የሚያበረታታው ማንም አክሊሏን እንዳይወስድባት ያላትን አጥብቃ እንድትይዝ ሲሆን፤ ለዚህም በማበረታቻነት የሚናገራት ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ በቶሎ እንደሚመጣ በመንገር ነው።
7. በቁ12-13 ያለው ክፍል በአጠቃላይ የሚናገረው ነገር ድል መንሳትንና ድል ነሺ የሚያገኛቸውን ነገሮች አስመልክቶ ነው። ድል የነሳው በእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ውስጥ አምድ ያደርገዋል ከዚያም ከቶ አይወጣም፣ የእግዚአብሄርንና የአዲሲቱን ኢየሩሳሌም ስም በእርሱ ላይ ይጽፋል የሚሉት ናቸው።
8. እርሱ የከፈተውን መዝጋት ወይም ደግሞ እርሱ የዘጋውን መክፈት ማንም አለመቻሉ በቃሉ ውስጥ ይሆናል ወይም አደርገዋለሁ ብሎ የነገረኝን ነገር ማንኛውም ሃይል ሊያስቀረው እንደማይችልና የህይወቴ አቅጣጫ በእርሱ ብቻ እንደሚወሰን ስለሚያረጋግጥልኝ ትልቅ ተስፋ ይሰጠኛል።

# ጥናት ሰባት ራዕ 3፡14-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጌታ ለሎዶቅያ ቤተ ክርስትያን ራሱን ያስተዋወቀባቸው አራት ስሞች፡ አሜን የሆነው፣ ታማኝ ምስክር የሆነው፣ እውነተኛ ምስክር የሆነውና፣ የእግዚአብሄር ፍጥረት ገዥ የሆነው የሚሉት ናቸው።
2. የሎዶቅያ ቤተ ክርስትያን ትኩሳትዋ ሲለካ ትኩስም አይደለችም ወይም ቀዝቃዛም አይደለችም፤ የቤተ ክርስትያኒቱ መንፈሳዊ ትኩሳት የተለካው በኢየሱስ በራሱ ሲሆን የሰው ሁሉ ትክክለኛው መንፈሳዊ ትኩሳቱን ሊለካና ሊመዝን የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው።
3. ቀዝቃነትን ኢየሱስ የትኩስነትን ያህል ይወዳል ማለቱ ሳይሆን፤ ቤተ ክርስትያኒቱ በመሃል ባትሰፍርና ትክክለኛ ያለችበትን ሁኔታ ለየሱስ ብታሳውቅ ወደ ትኩሳት ልትመጣ የምትችልበትን መፍትሄ ማግኘት ትችል እንደነበረ ሲያስገነዝበን ነው።
4. በቁ17 መሰረት የሎዶቂያ ቤተ ክርስትያን ስለራሷ ያላት አመለካከት ኢየሱስ ለእርስዋ ካላት ጋራ በጣም የሚቃረን ነው፣ እሷ ኃብታምና ባለጠጋ ነኝ አንዳችም ነገር አያስፈልገኝም ትላለች፣ ኢየሱስ ግን ጎስቋላ፣ ምስኪን፣ ድሃ፣ እውርና የተራቆትህ ነህ በማለት ይናገራል። እኛም ኢየሱስ ያየውን ቢነግረን እንጂ እኛ ስለራሳችን የምናየውና የምናስበው በአብዛኛው የተጣመመ ነው።
5. ይህች ቤተ ክርስትያን ያለባትን ችግር ለማረም ከኢየሱስ የተሰጣት ምክር ሃብታም ለመሆን በእሳት የነጠረ ወርቅ እንድትገዛ፣ እራቁትነት ሃፍረት እንዳይታይ ነጭ ልብስ እንድትለብስና፣ አጥርታ ማየት እንድትችል ደግሞ ዓይኗን በኩል እንድትኳል ነው የሚመክራት።
6. ኢየሱስ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስትያን በተግሳጽ አድርጎ የሰጠው ምክር ሁሉ ምንጩ በቁ19 ላይ እንደምናነበው እርሱ የሚወዳቸውን እንደሚገስጽ ነው የሚናገረው። የሎዶቂያ ቤተ ክርስትያን በቁ19 ላይ እንድትወስዳቸው የተነገሯት ሁለት ነገሮች፤ አንደኛው እንድትተጋ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ንስሃ እንድትገባ የሚሉት ናችው።
7. በሎዶቂያ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ኢየሱስ ያለው ስፍራ ከቁ20 እንደምናየው እርሱን እንዳስወጡትና የሚገኘው በደጅ እንደሆነ ሲሆን እንዲያስገቡትም ማሳሰቢያውን ያሰማል።
8. ለእያንዳንዱ ሰው ሃሳቡን እንዲገልጽ ጊዜ ይሰጠው።